


# የኢሕአግ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በታላቋ ብሪታኒያ መቋቋሙን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

የወያኔ ዘረኛ ቡድን የአፓርታይድ አገዛዝ ስርኣቱን በማራመድ የኢትየዮጵያን ሕዝብ ከፋፍሎ፤ አፍኖና እረግጦ በባርነት በሚገዛበት በዚህ ወቅት ነጻነት ያለ መስዋትነት እንደማይገኝ የተገነዘቡ አገር ወዳድ አርበኞች በኢትየዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ስር ተደራጅተው፤ እምቢ ለነጻነቴ፤ እምቢ ለሀገሬ፤ በማለት እስከፍንጫው ከታጠቀ የወያኔ ሰራዊት ጋር በዱር በገደሉ በማወደቅ ላይ ይገኛሉ።

ጀግኖች አርበኞች ለኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት ክቡር ህይወታቸውን አሳልፈው በመስጠት ከወያኔ ጦር ጋር በሚዋደቁበት በዚህ ፈታኝ ወቅት **የኛስ ሃገራዊ ድረሻ ምን መሆን አለበት ብሎ ነጻነት ወዳድ ህዝብ እራሱን መጠይቅ ይገባዋል**። ስለሆነም የብሄራዊ ነጻነት ትግል ያለ ሕዝባዊ ተሳትፎ ግቡን እንደማይመታ የተገነዘብን በታላቋ ብሪታኒያ የምንገኝ ሃገር ወዳድ ኢትዮጲያውያኖች ኖቬምበር 23 ቀን 2008 ዓ/ም እና ዲሴምበር 7 ቀን 2008 ዓ/ም ባደርግናቸው ስብሰባዎች የወያኔን ተፈጥሮና ባህርይ፤ የሃገራችንን ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታና የጀግኖች አርበኞችን ተጋድሎና መስዋእትነት በጥልቅ በመፈተሽና በመርመር፤ ዘረኛውን ስርአት ለማስወገድ የኢትየዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር (ኢሕአግ) የመረጠው የትግል ስልት ትክክለኛነት በሚገባ አረጋግጠናል።

ስለሆነም ለግንባሩ ትርጉም ያለው ድጋፍ ለመስጠት መደራጀት አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን በመረዳትና የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ፤ ዲሴምበር 7 ቀን 2008 ዓ/ም የኢትየዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የታላቋ ብሪታኒያ የድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ተቋቁሟል። አስተባባሪ ኮሚቴውም በዴሞክራሳዊ መንገድ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አበላትን በመሰየም የስራ ክፍፍል አድርጎ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሩን ለኢሕአግ አባላት፤ ደጋፊዎችና ለዲሞክራሲ ስርዓት እውን መሆን ለሚታገሉ ወገኖች ሁሉ ይፋ ስናደርግ በታላቅ ደስታ ነው።

ሃገራችን ኢትዮጲያ የጀግኖች ያለ በምትልበት በዚህ ወቅት ኢሕአግ ወያኔን በሚገባው ቋንቋ በማነጋገረ፤ የቁርጥ ቀን ደራሽነቱን በማሳየቱ ያለንን አክብሮትና አድናቆት እየገለጽን በዚህ አጋጣሚ በሌሎች ሃገሮች የምትገኙ ሀገር ወዳድ ኢተዮጲያውያኖች፤ ተመሳሳይ አቋም በመውሰድ ለግንባሩ ሙሉ ድጋፋችሁን እንድትሰጡ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

አንድነት ኃይል ነው!!
የኢሕአግ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በታላቋ ብሪታኒያ
ዲሴምበር 2008

Email: info@eppfonline.org: Website: www.eppfonline.org